# ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

### ከአቶ ዋሴ መኖሪያ ቤት ግቢ

## <u>ትዕይንት አንድ</u>

1. ከግቢው ውስጥ እና ከቤቱ በረንዳ ላይ

   1.1 ጽዳት በጎደለው ግቢ ውስጥ - ሦስቱ የአቶ ዋሴ ልጆች

   ( ፍቃደ የ14 ዓመት÷ጽጌ የ13 ዓመት እና ቤቲ የ10 ዓመት) ሲጫወቱ ይታያሉ

   1.2 ከበረንዳው ላይ ወ/ሮ ሽታዬ ከዱካ ወንበር ላይ ተቀምጠው ከኋላቸው ከብርኩማ ወንበር ላይ በተቀመጠች በቤት ሠራተኛቸው በወ/ት አማረች ሹሩባ ይሠራሉ (ግማሽ ፀጉራቸው እስካሁን ተሠርቶ ግማሹ በመሠራት ላይ ነው::

አቶ ዋሴ - በተከፈተው የሳሎን በር መንገድ ለመሄድ እንዳሰቡ ጸዳ ያለ ልብስ ለብሰው ከዘራቸውን እንደያዙ ሲወጡ ይታያሉ

ወ/ሮ ሽታዬ - መለስ ብለው ሲያዩአቸው ደንገጥ ብለው ኧረግ ደሞ ወዴት ሊሄዱ ነው የተሞሸሩት?

ዋሴ - /በደረሱበት እየቆሙ በመገረም/ እንዴት? ... አንቺ እኮ እንዲያው ልብ እሚባል አልፈጠረብሽም?

ሽታዬ - ማን? እኔው!?

ዋሴ - እና ታዲያ? ይሄውና ትናንትና ማታ... ያንን ጓደኛችንን መጠየቅ አለብን ተባብለን - ከአቶ ደመረ ጋር ስንቀጣጠር አጠገባችን ሆነሽ የሰማሽውን ልትረሽው

ሽታዬ - ወይ በሞትኩት.../እየሳቁ/ እኔ እኮ ሌላ መስሎኝ እንጂ እሱንማ አ. ም

ዋሴ - /ከበረንዳው እየወረዱ/ ኧ-ረ-ዲ-ያ- እንዳው ዝንተ ዓለምሽን ልበቢስ

እንደሆንሽ - ሆ-ሆ-ሆይ/ እየሳቁ - ወደ ግቢው በር ያመራሉ.../ /

ከግቢው በር ወዲህ ሦስቱ ልጆች ሲጫወቱ ይታያሉ/

ቤቲ- / የአቶ ዋሴ መምጣት ስትመለከት ጨዋታዋን አቋርጣ እና -

ከወንድምና ከእህቷ መሀል ወደ አባቷ እየሄደች/ እንዴ አባዬ ... እኔም...

እኔም አብሬህ እሄዳለሁ።

ዋሴ - ምን? ደግሞ ወዴት እንደምሄድ አወቅሽና ነው?

ቤቲ - ኧ- ረ- ኧ- ረ እና ጋሽዬን

ጽጌ- /አቋርጣት/ አሃ... እነ ጋሽዬን ልትቀበል አይደል?

ዋሴ - /በደነገጠ ጥርጣሬ እያሰቡ.../ ምን... እ.ና... እና ጋሽዬን

ፍቃደ - እናስ... በቀደም ለታ ከባለቤቱ ጋር ከአዲስ አበባ የሚመጡት

ዛሬ ነው ብለሽን አልነበር?

ዋሴ - /በድንጋጤ እየተርበተበቱና ወደ በረንዳው ዞረው በመጣደፍ እየሄዱ/ ጉ..ድ..ና

... ጅራት... ማ.. ን.. ማነሽ አንቺ ... ሽ.. ሽ...ታ..ዬ?

ሽታዬ - /አቀርቅረው ከሚጎነጎኑበት ቀና ብለው እያዩአቸው/ እ...? አ..አ..ቤ.ት

ዋሴ - ዛሬ ... ዛሬ ቀኑ ... ማን... ማን

ሽታዬ - /ደንገጥ እያሉ/ ኧረግ - ሰራዬውን ምን ነካብኝ

ዋሴ - መሃ መ መድኃኒዓለም አይደል እንዴ?

ሽታዬ - /በመጠራጠር እያሰቡ/ አ..አ..አዎን.. ምነው?!

ዋሴ - /በንዴት እያፈጠጡባቸው/ ም. ነ. ው?!

ሽታዬ - /ግራ በመጋባት/ ወይ በሞትኩት... አሁን ባሁን ምን ነካብኝ

ዋሴ - / ቱግ/ የተነካሽውስ አንቺ

ሽታዬ - በ. ጉ. ዴ.. መጣ

ዋሴ - እናስ አንቺ? እስቲ አሁን ማን ይሙት ... እነ ተመስገን ከአዲስ አበባ ድረስ

የሚመጡት ዛሬ መሆኑ እያወቅሽ ... ዝም ብዬ ስሄድ ታይኛለሽ?

ሽታዬ -/ ከተቀመጡበት ራሳቸውን ይዘው እተርበተበቱና እየተነሱ ክፉኛ በደነገጠ

ስሜትና ልሳን / ወይ.. ወይ.. ወይ ምነው … ምነው ዋሴ ጉድ አረጉኝ

ዋሴ – / በንዴት እየተወራጩና ከዘራቸውን ጥለው ጋቢያቸውን እያወለቁና

እየተርበተበቱ / ኧረዲያ … ሁሌም በእኔ ላይ እንዳሳበብሽ – ጉድ ልጆቹ

አቤት እስቲ አሁን አንድም ነገር ሳልዘጋጅ – ማናችሁ ልጆች

ሽታዬ – / ወደ ሳሎኑ በር እየሄዱ … /ጉድ – ጉድ … ጉድ/ ከበሩ ጋ ደርሰው እየቆሙ

እያሰቡና – ወደ አማረች እየዞሩ / ም…ን…ማን ወይ በሞትኩት …ማን…

ማነሽ አንቺ አማረች

አማረች – / በድንጋጤ ላይ እንደተቀመጠች ሳትነቃነቅ ስታያቸው ቆይታ …/ አ..አቤት

እትዬ

ሽታዬ – ለ… ለ… ለመሆኑ … ያንን ጤፍ አስፈጭተሽዋል ወይስ ገና ነው?

አማረች – ኧረ እትዬ …ገ … ገ… ገና መቼ ተበጠረና

ሽታዬ – እግዚኦ ያንተ ያለህ … / እያፈጠጡባት/ ምነው አንቺ…/ ቱግ ብለው

እያፈጠጡባት በማመናጨቅ/ ተነሽ እኮ ነው የምለው ደሞ ተቀምጣ

ታየኛለች እንዴ!!/ ወደ በሩ እየተርበተበቱና እያጉተመተሙ ሄደውና

ገብተው ይሰወራሉ

አማረች – / ከተቀመጠችበት በድንጋጤ ተፈናጥራ እየተነሳች – እቃዎቹን ትሰበስባለች/

# ትዕይንት ሁለት

2. /በፈጣን እንቅስቃሴ በሠላሳ ሴኮንድ ዕድሜ ውስጥ የሚሠራ/

2.1 /ከዚያው ከግቢው ውስጥ እና ከቤቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎችና ክፍሎች ውስጥ የቤተሰቡ አባላት በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተጠምደው በመፈራረቅ ይታያሉ/

አማረች - /ጤፍ ስታበጥር እና ጤፉን ለማስፈጨት ስትዘጋጅ፥ በተጨማሪ የሽሮ እህል ወዘተ...

ወ/ሮ ሽታዬ - / ከሴት ልጆቻቸው ጋር በመከፋፈል - እሳት ሲያነዱ፥ ውሃ ሲጥዱ፥ እቃ ሲያጥቡ፥ ሽንኩርት ሲከትፉ...

አቶ ዋሴ - ግቢ ሲያጸዱ፥ የሳሎኑን ሶፋና ወንበሮች አውጥተው ከበረንዳው ላይ ሲደረድሩ፥ ሳሎኑን ሲያጸዱ ወዘተ...

ቤቲ - /እንጨት ስትፈልጥ - ከአባቷ ጋር ግቢውንና ቤቱን ስታጸዳ ወዘተ...

2.2 / በፈጣን እንቅስቃሴ ከላይ የታየው ትዕይንት ማብቂያ አካባቢ... አቶ ዋሴ ከበረንዳው ላይ ላብ በላብ እንደ ሆኑ - የሶፋ ወንበሮቹን እያራገፉ ካጸዱ በኋላ የሶፋዎቹን ልብሶች ያለብሳሉ

አማረች - / ስታበጥር የቆየችውን እህል በሁለት ከረጢት አስራ አንዱን በትከሻዋ እንደ ተሸከመች ሌላውን በአንድ እጇ አንጠልጥላ ... እንደያዘች... ከቤቱ ጓሮ ስትመጣና ... እነ ዋሴን አልፋ ወደ ግቢው በር በሩጫ እርምጃ ስትሄድ ትታያለች/

ጽጌ - /በትንሽ ከረጢት እህል ተሸክማ... አማረችን ትከተላለች/

/ ከግቢው በር ላይ/

አቶ ደመረ - / የተዘጋውን የግቢ በር ከፍተው በመዝናናት ስሜት ጥርሳቸውን እየፋቁ

ይገቡና ቆም ብለው በሩን እየዘጉ - ወደ ግቢውና ወደ በረንዳው ሲመለከቱ-

በአማረች ሁኔታ በተዝረከረኩ ዕቃዎች እና በአቶ ዋሴ ሁኔታ ይደነግጡና

ወደ በሩ በመምጣት ላይ ወዳለችው ወደ አማረች ጠጋ ይሉና ያናግሯታል::

አማረች - /ምላሽ በመስጠት ምትክ - መጣደፏን እንደ ቀጠለች እያጉተመተመች

አልፋቸው ሄዳ በግቢው በር ወጥታ ትሰወራለች/

ጽጌ - / አማረችን ተከትላት እንደ መጣች ትወጣለች/ ከላይ ይሰማ የነበረው ፈጣን ሙዚቃ

ድምጽም እየቀነሰ ወርዶ ይጠፋል.../

/ከሙዚቃው ጋር ፈጣን እንቅስቃሴ ይታይ የነበረው የቤተሰቡ እንቅስቃሴ -

ወደ ትክክለኛ ቦታው ይመለሳል/

አቶ ደመረ - /በሚያዩት ነገር ግራ እንደ ተጋቡ ሰዓታቸውን ያዩና ወደ ዋሴ እየተራመዱ

/ጉድና ጅራት ... ማኖት አንቱ ዋሴ

ዋሴ - ሥራቸውን አቋርጠው የግንባራቸውን ላብ እየጠረጉ ቀና ብለው እያዩዋቸው

ወይ በሞትኩት ደምዬ መጣህልኝ የኔ ጌታ

ደመረ - እንዴት?! እኔ ካሁን አሁን ትመጣለህ ብዬ ስጠብቅህ አንተ ገና ትድበሰበሳለህ?

ዋሴ - ኧረ ተወኝ ...ኧረ ተወኝ ደሜ ተዋረድኩልህ እኮ

ደመረ - / በድንጋጤ የተዝረከረኩትን እቃዎችን እያዩ/ ም..ን..? እህ... እውነት ምንድን

ነው ይህ ሁሉ ትርምስ?

ዋሴ - ምነው እንዴ ይህ ባለው ጊዜ አዲስ አበባ ድረስ ሄጄ ያደረስኩት ልጄ እሱ እሱ ነው

ደመረ - /በድንጋጤ/ ወይ በሞትኩት ... ተመስገን እንዳይሆን!

ዋሴ - አዎን ... ደ... ም... ዬ

ደመረ - አቤት ያንተ ያለህ... ምን አጋጠመው በኔ ሞት

ዋሴ- አይ ... እሱማ ምን ይገጥመዋል ... ይሄውና ባለፈው ጊዜ...በስልክ ደውሎ ከሙሽራዋ

... ማለት ከባለቤቱ ጋር በዛሬዋ ቀን እንደሚመጣ ከነገረኝ በኋላ እርስት አድርገነዋል

... /እቃዎቹን እየጠቆሙ/ ይሄውልህ

ደመረ - / አቋርጠውት እየሳቀ / አ -ሃ- ሂ -ቂ- ቂ እና “ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ”

እንደሚባለው  አ -ሃ- ሂ -ቂ- ቀ / ሆዱን ይዞ ይስቃል

ዋሴ - / በመመናጨቅ/ ኧረ ዲያ -አሁን በኔ ላይ መሳቅህን ትተህ -ይልቅ ምናለ

ብ-ታ-ግ-ዘ-ኝ

/አቋርጧቸው የመጨረሻውን ቃላቸውን ደርቦ የግቢው በር ተበርግዶ ሲከፈት

ይታያል/ አቶ ዋሴ ንግግራቸውን አቶ ደመረም ሳቃቸውን አቋርጠው በመደንገጥ

ወደ ግቢው በር ዞረው እያዩ ያፈጣሉ

ጽጌ - / በተከፈተው በር እየሮጠች፥ እየገባች፥ እያለከለከች እና ወደ አባቷ እየሮጠች/

አባ ... አባዬ እነ .. እነ ጋሼ እየመጡ ነው

/ሙዚቃ ይገባል/

ዋሴ - /ክፉኛ ደንግጠው -በእጃቸው የያዙትን እየጣሉ ከኋላቸው ካለው ወንበር ላይ

በቁማቸው ወርደው እንደ ደነዘዙ ይቀመጣሉ/

ደመረ - /በተቀመጡበት እንደ ደነገጡ ወደ ዋሴ ዞረው ያያሉ/